FAQ Sections
Introduction
XML Overview
XML FAQ
Glossary
Resources

መግቢያ
ኢማላ ሲሉ
ኢማላ ተመም
ምእላደ ቃላት
ምንጭት
መነሻ ገጽ

ምእላደ ቃላት

ሃቴማላ (HTML)

«**ሃቴማላ**» ፥ ሰነዶች በዌብ ገጽ ላይ እንዴት እንደሚቀመጡና መልካቸውስ ምን መምስል እንዳለበት መግለጫ መንገድ ነው ። የዌብ ገጽ ስፋት ፥ የፊደላት አይነትና ቀለም ፥ ያርስቶችና ያንቀጾች አቀማመጥ ፥ ካንድ ነጥብ ወደሌላ መስፈንጠሪያ መንገዶችንና የመሳሰሉትን ይገልጻል ። ባጭሩ ፥ ሃቴማላ የገጽ መግለጫ ቋንቋ ነው ።

ሆሄ ፥ ሆሄያት (ለብዙ) (character)

ማንኛውም ፊደል ፥ የንባብ ምልክት ፥ ሥርዓተ-ነጥብ ፥ ቁጥር ፥ ምልክት ። ለምሳሌ ፦ ሀ ፥ ለ ፥ ሐ ፥ መ . . . ፤ 1 ፥ 2 ፥ 3 ፥ . . . ።

ጎላፍ (left-margin)

ከግራ ጠርዝ እስከ ጽሑፍ መወደቂያ ያለው ክፍት ቦታ ።

ሞጎት ፥ ሞጎያት (ለብዙ) (white space)

በፊደላት ፥ መካከል ያለ ክፍት ቦታ ።

መሣሪያ (tool)

ፕሮግራም ጸሐፊዎች የተለያዩ መፍትሄዎች ለመገንባት የሚጠቀሟቸው

ፕሮግራሞች ። ለምሳሌ ንባብ መከተቢያ ።

መረጃ ፥ (ዴታ) (data)

ስለተካሄደ ወይም ስለተከናወነ ድርጊት ያልተበረዘ ቃል ። ስለቦታ ፥ ስለሰው ልጅ ፥ ስለጠፈርና የመሳሰሉት ያልተበረዘ ቃል ። የአፍሪካ የህዝብ ቁጥር ፥ ዓመታዊ የኑሮ ገቢ ፥ መልክአ-ምድርና የመሳሰሉት እርግጠኛ መረጃዎች ናቸው ። የሰው ልጅ ስም ፥ ዕድሜ ፥ ቁመት ፥ መኖሪያ ቦታና ሌሎችም እንደዚሁ መረጃዎች ናቸው ። ባጠቃላይ መረጃ ማለት እውን ቃል ስለቦታ ፥ ስለድሪጊት ፥ ስለተፈጥሮ ፥ ስለሰባዊነት እንዲሁም ሌሎች ።

መቃኛ ፕሮግራም (browser)

ዌብ ገጾችን ለማንበብ ወይም ለማተም የኢንተርነት ተጠቃሚዎች የሚገለገሉት ።

መነሻ ገጽ (home)

የማንኛውም ዌብ ገጽ የግንባር ክፍል ፤ ገጹ ሲከፈት መጀመሪያ የሚመጣው እይታ ።

ሜታዴታ (metadata)

ሜታዴታ ሲሉ ፥ ባጭሩ የመረጃዎች መረጃ ወይም የዴታዎች ዴታ ለማለት ነው ።

መዋቅር (structure)

1ኛ ያካል አቋቋም ፥ አወቃቀር ከላይ እስከ ታች ። 2ኛ በዲስክ ላይ ወይም በሜሞሪ ውስጥ መረጃዎች ሲሰፍሩ የሚኖራቸው አሠፋፈር ፥ አገነባብ ። በኮምፕዩተር ሳይንስ ዓለም ፥ የይዘቶች አጠነቃቀር በዛፍ ይመስላል ። የዛፍ አቋቋም ፥ ሥርን ፥ ግንድንና ፥ ቅርንጫፎችን ይጨምራል ። እንደ መሰላል ዛፍን መውጣትና መውረድ ይቻላል ። ይዘቶችን በዛፍ አወቃቀር ማጠናቀሩ እጅግ ብዙ ጥቅሞች አሉት ።

ሲ++ (C++)

በቢየርን ስተሮቭስተሩፕ (Bjarne Stroustrup) እአአ በንጋቱ 1980 ላይ የተፈጠረ ፕሮግራም መጻፊያ ቋንቋ ነው ። ባለፉት አያሌ ዓመታት ፥ ሲ++ ከፍተኛ ተቀባይነትንና ዝናን ያተረፈ ቋንቋ ነው ። የዓለም አቀፍ የስታንዳርድ ድርጅት የቋንቋው የበላይ ጠባቂ ሲሆን ፥ ማንኛውም ሰው ያለምንም ጫናና ክፍያ ቋንቋውን ለተፈለገው ጉዳይ መጠቀም ይችላል ።

ሰርቨር (server)

በኮምፕዩተር መረብ ውስጥ ፥ ለተከታይ ኮምፕዩተሮች ልዩ ልዩ ግልጋሎት ሰጪ ኮምፕዩተር ፤ አባወራ ኮምፕዩተር ።

ሰነድ-አይነት-ደንጋጊ (ሰአደ) (DTD: Document Type Definition)

በኤማላ አዲስ የምልክት ቋንቋ መፍጠሪያ ፋይል ወይም ክፍል ።

ሠንጠረዥ (table)

በረድፍና ባምድ የተሸነሸነ ፤ ነገሮችን በጐንና በቁም ያሠለፈ ፤ የጽሑፍና የሥዕል አቀማመጥ ። ሠንዘረዥ በመስመር ሊታጠር ወይም ላይታጠር ይችላል ።

ሲ/ኤስ/ኤስ (CSS)

የዓላም-አቀፍ-ዌብ ኮንሰርሽየም ሥራ ነው ። ሃቴማላ (HTML) መስጠት የማይችለውን የጽሑፎችንና የሥእሎችን አቀማመጥና መልክ ማዘጋጂያ «ገጽ ገላጭ ቋንቋ» ።

ሥምሪት (run program)

ኮምፕዩተሮች ላይ ፕሮግራሞችን ለሥራ ማንቀሳቀስ ፥ ማስነሳት ፥ ማራመድ ።

ስላሽ (slash)

የላቲን ሆሄ (/)

ሥርዓተ-ነጥብ (panctuation)

በሥርዓተ-ፊደል ውስጥ የሚገኙ የንባብ ምልክቶች ፤ ለምሳሌ ! ፤ ፥ ። ፣ « »

ሶፍትዌር (software)

ኮምፕዩተር ላይ ሥራዎችን ለማካሄድ የሚያስችሉ ፕሮግራሞች ካሠራር መመሪያዎች ጋር ።

ስክ-ንባብ (string)

ካንድ በላይ ሆሄያት የያዘ ። ቃል ወይም ኢ.ቃል ፥ ሐረግ ወይም ኢ.ሐርግ ፥ ዐርፍተ-ነገር ወይም ኢ.ዐርፍተ-ነገር ። ስክ-ንባብ የግድ ቃል ፥ ሐረግ ወይም ዐርፍተ-ነገር እንዲሆን አይገደድም ። ለምሳሌ ፥ ሀሀሀሀ ፥ ለለለለ ፥ ሐሐሐሐ እና ሀለሐመ ስክ-ንባብ ናቸው ።

ረድፍ (row)

በጐን የተደረደረ ፥ የተሠለፈ ፥ የተቀመጠ ። በጋድም የተሰካካ ፥ የተገጣጠመ ።

ቃለ-ኖኅት (word separator)

ቃላት ለመለያየት የሚገባው ክፍት ቦታ ። የሁለት ነጥብ እኩሌታ ።

ቃለ-መመሪያ (statement)

ፕሮግራም ሲጻፍ የሚሰነዘረው እያንዳንዱ መመሪያ ።

ቃለ-ምልክት (tag)

1ኛ በኤማላ ሰነዶች ውስጥ ይዘቶቹን ገላጭ ፍሬ ቃላት ፤ በ (<>) ምልክት የሚታጠሩት ። በሃቴማላ ቃለ-ምልክቶች ፥ ተነባቢው ነገር እንዴት መቀመጥ/መታይት/መጻፍ/መደርደር እንዳለበት ለመቃኛ-ፕሮግራም እገዘ የሚሰጡ 2ኛ ክፋች ቃለ-ምልክት (open tag) ፦ እንደ <

ቃለ-አንቀጽ ፦ አጎጽሮተ-ቃላትንና ቅጽል ስሞችን ይመሠርታል ።

<!ENTITY aau "Addis Ababa University">

ቃለ-አዋጅ (declaration)

ፕሮግራም ሲጻፍ መረጃ/ዴታ መጠበቂያ የሜሞሪ ክፍል መክፈቻና መሰየሚያ ቃል ።

ቃል (word)

አንድ ወይም ካንድ ፊደል በላይ የያዘ ፥ ትርጉም ያለው ።

ቀኝ ኧንግል ብራኬት (right angle bracket)

የላቲን ሆሄ (>)

ባለሰነድ-ሠራሽ (customize)

በኤማላ ሰነዶች አዘጋጆች የሚፈጠር ቃለ-ምልክትና የመሳሰለው ።

ተመም (faq)

የኢንተርነት ውይይት መድረኮች ውስጥ ተመሳሳይ ጥያቄዎች በጣም ተደጋግመው ይቀርባሉ ። በዚህ የተነሳ የሚፈጠረውን መጨናነቅ ለመቀነስ እንዲሁም የጠያቂዎችን ፍላጐት ለማርካት ፥ ተደጋጋሚ መጠይቆችና መልሶቻቸው በተፈለገው ጉዳይ ይዘገጃሉ ። እንደዚህ አይነት ጽሑፎች/ሰነዶች ተደጋጋሚ መጠይቆችና መልሶች (ተመም) ወይም በእንግሊዘኛ Frequently Asked Questions ይሏቸዋል ።

ታብ (Tab)

የተመጠነ ክፍት ቦታ ፈጣሪ የኪቦርድ ኪ ወይም ሆሄ ።

ተውላጠ-ቃል (variable)

ፕሮግራም ሲጻፍ መረጃ/ዴታ መጠበቂያ የሜሞሪ ክፍል ፥ አይነት ፥ መጠንና ስም ያለው ።

ትልቁ/ትንሹ ሆሄ (ፊደል) (uppercase/lowercase letters)

በላቲን ሥርዓተ-ፊደል ውስጥ በሁለት መልክ የሚጻፉ ፊደላት አሉ። አነሱም ትልቁ ፊደል (uppercase/capital letters) እና ትንሹ ፊደል (lowercase/small letters) ናቸው። ትልቁ ፊደላት A, B, C, . . . , Z ሲሆኑ ፣ ትንሾቹ ፊደላት ደግሞ a, b, c, . . . , z ናቸው።

ነጠላ-ጥቅስ-ምልክት (single quote)

ጥቅሶች መከለያ የላቲን ንባብ ምልክት (' ') ።

ንባብ (text)

ንጹሕ አንድ ወይም ካንድ በላይ ቃላትን የያዘ የወረቀት ፣ የቃል ወይም ኤለክትሮኒካዊ ጽሑፍ ።

አጎጸሮተ-ቃል (abbreviation)

አንድ ወይም ካንድ በላይ የሆኑ ቃላትን ባጭር ቃል መወከል ለጽሑፍ ፣ ለንግግር ። ዓለም አቀፍ ዌብ (ዓአዌ) ፣ አዲስ አበባ (አአ) ፣ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር (ኢተማ) ፣ ወዘተ ።

ዐረፍተ-ነገር (sentence)

በሰዋሰው ህግ መሠረት ታነጸው ፣ ባራት ነጥብ የተደመደሙ ቃላት ።

አንቀጽ (paragraph)

ካንድ በላይ ዐረፍተ-ነገሮችን የያዘ የገጽ ጽሑፍ ።

አዲስ መስመር (new line)

1ኛ አዲስ አንቀጽ (paragraph) መጀመሪያ ። 2ኛ መስመር አጣፊ ሆሄ/ሆሄያት ።

አሳሽ ኢንጅን (search engine)

ኢንተርነት ውስጥ ሰነድ መፈለጊያ ዌብ ገጾች ፥ እንድ www.google.com ፥ www.altavista.com እና የመሳሰሉት ።

አብይ-አንቀጽ (XML element)

አብይ-አንቀጽ ፦ ያንድን ተናጠል ይዘት መጠሪያ ፥ የይዘት አይነት ፥ እንዲሁም በክልሉ መሰፈር ያለባቸውን ሌሎች አንቀጾች ይመሠርታል ። ለምሳሌ ፦

```
<!ELEMENT periodic-table (element)+>
```

አገናኝ-ቃል (hyperlink)

የዌብ ገጽ ሰነዶች አስተሳሳሪ ፥ አስተባባሪ ፤ ከገጽ ወደ ገጽ አሸጋጋሪ ። ይህ ቃል ሰንምርምር ገጽ ወደ ሰነምርምር ገጽ መሰፈንጠሪያ ነው ።

ዓለም አቀፍ ዌብ ኮንሰርሽየም (W3C: World Wide Web Consortium)

በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ፥ በዌብ ፋጣሪ ሊ. በርነር-ሊ. የሚመራ ፥ የሃቴማላ (HTML) ፥ የኤማላ (XML) ፥ እና አያሌ ሌሎች ሥራዎች የበላይ ጠባቂ ድርጅት ። የዓለም አቀፍ ዌብ ኮንሰርሽየም ገጽ http://www.w3.org ነው ።

ኤማላ (XML)

የExtensible Markup Language አጎጽሮተ-ቃል ። በተለምዶ XML የሚለው አጎጽሮተ-ቃል ባማርኛ ኤከስ/ኤም/ኤል ይሆናል ። ይህን የመጨረሻ ቃል እንዲያጥር ቢደረግ ኤ/ክስምል ይመጣል ። ሌላው አማራጭ ለራሱ ለExtensible Markup Language እኩሌታ ያማርኛ ትርጉም ማበጀት ነው ። ተስፋፊ አካላይ ቋንቋ ፤ ተስፋፊ አመላካች ቋንቋ ፤ ወይም የተስፋፊ መቀነፊያ

ቋንቋ ፤ ለሙከራ ያህል ጥሩ ናቸው ። በአጎጽሮተ-ቃል መልካቸው በተራ ፦ ተ/አ/ቋ እና ተ/መ/ቋ ይመጣሉ ። ስየማ ውስጥ አሁኑኑ ከመግባት ፥ በኤማላ መርጋቱ ለጊዜው ያመቻል ።

ዓምድ (colmn)

ገጽ ላይ በቁም የተሸነሸነው ንባብ ። በቁም የተሸነሸነው የሠንጠረዥ አካል ።

ዕሴት (value)

በተውላጠ-ቃለ ወይም በሜሞሪ ክፍል ውስጥ የሚጠበቅ ቁጥር ፥ ሆሄ ፥ ስክንባብ ፤ ባጠቃላይ ዋጋ ፥ መጠን ፥ ተቆጣሪ ፥ ተተማኝ ።

እይታ ፥ ገጽታ (screen)

ጹሑፎች ፥ ግራፊክሶችና የመሳሰሉት የሚታዩበት የኮምፕዩተር ሞኒተር ክፍል ፤ ፊት ለፊት ያለው ።

ኮምፕዩተር መረብ (computer network)

በሽቦ ፥ በስልክ ፥ በሳተላይት እንዲሁም በልዩ ልዩ ሞገድ ተሳስረው ለመገናኛ የበቁ የኮምፕዩተሮች ስብስብ ።

ዌብ ገጽ (web page)

በኢንተርነት የኤሌክትሮኒክ ሰነዶች ፤ ንባብ ፥ ግራፊክስ ፥ ድምፅ እና ሌሎች ነገሮችን የሚይዙ ። ለማንበብ ወይም ለማተም መቃኛ ፕሮግራም የሚጠይቁ ፤ በሃቴማላ ቋንቋ የተዘጋጁ ።

ዴታ አይነት (data type)

የቁጥር አይነቶች ፦ ሙሉ ቁጥር (integer) ፥ ፍሎት ቁጥር (float) ፤ ሆሄ (character) ፥ ቡሌን ፥ እውነት (true) ፥ ሐሰት (false) ። ቁጥሮች በመጠን ማለትም በሚይዙት የሜሞሪ ስፋትና ጥበት ይከፈላሉ ፥ ለምሳሌ ፦ byte ፥ short ፥ int ፥ long ፥ float ፥ double እና

የመሳሰሉት ።

ድርብ-ጥቅስ-ምልክት (double quote)

ጥቅሶች መከለያ የላቲን ንባብ ምልክት ("") ።

የግል ኤመልክት መድረክ (mailing-list group)

በኤለክትሮኒክ መልክት ልውውጥ ላይ የተመሠረተ ፥ ፍቃደኛ አባላትን ያቀፈ ፥ መልክቶች ላባላት ብቻ የሚሠራጭበት ፥ የራሱ የሆነ አስተዳዳሪ ያለው ፥ የግድ የኢንተርነት ቁራኛ ያልሆነ ፥ ከሁሉም በላይ ባንድ ዓላማ ላይ የተመሠረተ የግል ስብስብ ነው ።

ዩንኮድ (Unicode)

1ኛ ፊደላትን ኮምፕዩተር ውስጥ ለማስገባት ወይም በመስመር ለመለዋወጥ ፥ ፊደላቱ የሚያሻማ ኮድ መሰየም አለባቸው ። ኮምፕዩተሮች ፊደላቱን የሚለዩት በዛ ኮድ እንጂ በመልካቸው አይደለም ። ኮዶቹ የሚሠሩት ከቁጥር ነው ። አያሌ የኮድ ስልቶች በሥራ ላይ ውለዋል ። በዚህ የተነሳ አለመግባባት ፥ አለመጣጣም ፥ ግጭት አለ ። ዩኒኮድ አንድ ወጥ የሆነ ስልት ወይም ሠንጠረዥ ለመገንባት የሚሞክር መደበኛ ወይም ስታንዳርድ (standard) ነው ። 2ኛ ዩኒኮድ መደበኛ (Unicode standard) ፦ ለኮምፕዩተሮች ሥራ ፥ የዓለም ቋንቋዎች ፊደላትን በኮድ የሚወክል ሠንጠረዥ ፤ መደበኛ ። 3ኛ ዩኒኮድ ኮንሰርሽየም (Unicode consortium) ፦ በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ፥ ፊደላትን ኮድ የሚሰይም ዓለም-አቀፋዊ (ዓለማቀፋዊ) ተቋም ነው ። በዩኒኮድ መሠረት እያንዳንዱ ፊደል ሁለት ባይን የሜሞሪ ቦታ ይይዛል ።

ዩዝነት (Usenet)

በዓለም አቀፍ ደረጃ ፥ ኢንተርነት ላይ በፍቃደኛነት የተቋቋሙና የሚካሁዱ ኤመልክታዊ የውይይት መድረኮች ። ቁጥራቸው ከ30,000 በላይ ይሆናል ተብሎ ይገመታል ። ዩዝነት መድረኮች

ኢንተርነት መግባት ለሚችል ሰው ሁሉ ክፍት ናቸው ። ይዘታቸው ይፋ ነው ። ዩዝነት መድረኮች ውስጥ በተናጋሪነት ወይም ባዳማጭነት ለመሳተፍ ልዩ ፕሮግራም ይጠይቃል ።

ይዘት (content)

1ኛ በመያዣ ውስጥ የተቀመጠ ነገር ። 2ኛ በፋይል ውስጥ የተቀመጠ ጹሑፍ ፥ መረጃ ፥ ዌብ ሰነድ ፥ ቃላዊ-ሥዕል ፥ ቃላዊ-ድምፅ ፥ ወዘተ ።

የጥቅስ ምልክት (quotation mark)

የኢትዮጵያ ፊደል የጥቅስ ምልክት (« ») ።

ግልየት (right-margin)

ከቀኝ ጠርዝ እስከ ጽሑፍ መወደቂያ ያለው ክፍት ቦታ ።

ዴታቤዝ (database)

በኮምፕዩተር ማዕከላዊ መረጃ/ዴታ ማከማቻና ማስተዳደሪያ ስልት ።

ድንጋጌ (definition)

ያንድ ነገር ምንናማንነት ገለጻ ። ለምሳሌ ፥ የቃላት ትርጉም ፤ ይህ ምዕላደ-ቃላት ሊያደርግ እንደሚሞክረው ።

ጃቫ (Java)

በሰን ማይክሮሲስተምስ (Sun Microsystems) የተፈጠረ ፕሮግራም መጻፊያ ቋንቋ ። ባሁኑ ሰዓት ከፍተኛ ተወዳጅነት ያተረፈ ። ፕሮግራም ለመጻፍ አመቺ የሆነ ።

ገጽ መግለጫ ቋንቋ (page description language)

የጹሑፎች እንዲሁም የሥዕሎች አቀማመጥ መወሰኛ ቋንቋ ፥ እንደ ሃቴማላ ያለው ።

ግርጌ ማስታወሻ (footnote)

የገጾች የታችኛው ቦዶ ክፍል ጎዳግ ተብሎ ይጠራል ። በዚህ ሥፍራ ገጹ ውስጥ ያለውን ጽሑፍ ለመደገፍ የሚጻፍ ማብራሪያ ፥ ጥቅስ ፥ ማስረጃ ፥ አጣቃሽ ነገር ።

ግራ ኧንግል ብራኬት (left angle bracket)

የላቲን ሆሄ (<)

ጠባየ-እንቀጽ (XML attribute)

ጠባየ-እንቀጽ ፦ ያንድን አብይ እንቀጽ ጠባዮች ይደነግጋል ።

ፊደል (alphabet)

ከሀ--ፐ ፥ ከ0-9 ፥ የመሳሰለው ።

ፋይል (file)

1ኛ ማንኛውም ወደ ኮምፕዩተሩ የሚገባና የሚወጣ ነገር ፥ ዴታን ጨምሮ በፋይል ይጠናቀራል ። ፋይል የራሱ የሆነ ስም ፥ የይዘት አይነት ፥ የተፈጠረበት ቀን ፥ እንዲሁም መጠን አለው ። ለምሳሌ ፥ ኤለክትሮኒካዊ መልክቶች ከቦታ ቦታ የሚጓዙት በፋይል መልክ ተጠናቅረው ነው ። ዲስኮች ላይ ይዘቶች የሚሰበሰቡት በፋይል ነው ። ዌብ ላይ የምናያቸው ነገሮች በሙሉ የሚመጡት በፋይል መልክ ነው ። ያለፋይል ምኑን ከምን!!! 2ኛ ፋይል ከታታ (save file) ፦ ፋይልን ዲስክ ላይ መጻፍ ፥ መቅርጽ ፥ ወይም ማስቀመጥ ። ይዘቱ ተቀይሮ ሜሞሪ ውስጥ ያለን ፋይል ወደ ዲስክ መጻፍ ። 3ኛ ፋይል ግልበጣ (copy file) ፦ ካንድ ዲስክ ወደ ሌላ ፋይል መገልበጥ ወይም አንድን ፋይል በሌላ ስም መድገም ። 4ኛ ፋይል ሽግር (move file) ፦ ካንድ የዲስክ ቦታ ፋይል መሠረዝና ወደ ሌላ ቦታ መጻፍ ። 5ኛ ፋይል ሠረዛ (delete file) ፦ ከዲስክ ላይ ፋይል ማንሳት ፥ ማጥፋት ፥ መደምሰስ ።

ፎንት ፥ ሥርዓተ-ፊደል (font)

1ኛ ፊደል ፥ አጎዝ ፥ ሥርዓተ-ነጠብ ፥ አይነተኛ ምልክቶችን ያቀፈ ፤ 2ኛ አንድ አይነት መልክ ፥ መጠን ፥ ቀለም ያለው ፤ 3ኛ ጹሑፎችን የሞኒተር ገጽታ ላይ ለማሳያት ወይም ወረቀት ላይ ለማተም የሚያስችል ፤ 4ኛ የሆሄያትን መልክ በፎርሙላ የሚወክል ።

ፕሮግራም (program)

ልዩ ልዩ ተገባራትን ማለትም የጹሑፎች ፥ የዴታቤዝ ፥ የሥዕል ፥ የስፕርድሸትና ሌሎች ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ፥ በፋይል መልክ የተጠናቀረ መመሪያ ። ፕሮግራም ፥ በጃቫ ወይም በመሳሰሉት ቋንቋዎች ይጻፋል ።

ፕሮግራም መጻፊያ ቋንቋ (programming language)

ለኮምፕዩተሮችና ልዩ ልዩ መሣሪያዎች መመሪያ መጻፊያ ቋንቋ ። ጃቫ (Java) ፥ ሲ (C) ፥ ሲ++ (C++) እንዲሉ ።

ፓርሰር (parser)

የኤማላ ፓርሰሮች (parsers) ጥሳያትን አይጥሉም ። ፓርሰሮች የኤማላ ሰነድ በልተው (ሸንሸነው) ለተጠቃሚው ፕሮግራም የሚያቀርቡ የኮምፕዩተር ፕሮግራሞች ናቸው ። ለምሳሌ ፥ የመቃኛ ፕሮግራም አንድ የኤማላ ሰነድ ዌብ ገጽ ላይ ለማሳየት ፥ ይዘቱን መንጥሮ የሚያወጣለት የፓርሰሩ ፕሮግራም ነው ። ስለዚህ ማንኛውንም ለአቅመ-ሥራ የደረሰ የኤማላ ሰነድ ለሥራ ስናሰመራ ፥ የመጀመሪያው ሂደት በፓርሰሩ በኩል ማለፍ ነው ።

ፕሮግራም ጸሐፊ (program writer)

የፕሮግራም ቋንቋዎችን ተጠቅሞ ፕሮግራም የሚጽፍ ፤ ሞያው ያደረገ ።

. . .

smirmir@senamirmir.com

©Senamirmir Project, 2001